# አለሚቱና ገብሩ



1ኛ ክፍል

25-28ኛው ሳምንት

መጽሐፍ 9

# አለሚቷና ገብሩ

መጽሐፍ 9 | 1ኛ ክፍል | 25-28ኛው ሳምንት



ይህ አጋዥ የንባብ መጽሐፍ ከዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ. (USAID) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በፓክት ኢትዮጵያ (Pact Ethiopia) እና በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ የጋራ ትብብር ተዘጋጅቶ በሴቭ ዘ ቺልድረን (Save the Children) እና በትምህርት ሚኒስቴር ተሻሽሎ ታተመ::

The CC By license lets others distribute, adjust, and build upon this work, for free or commercially, as long as credit is given to the original creation. However, any changes from the original must be indicated.
For more info please refer: *https://creativecommons.org/licenses/*



አለሚቱና ገብሩ ጓደኞሞች ናቸው። አለሚቱ አይነስውር ናት። ገብሩ አለሚቱን እየመራ ወደገበያ ሄዱ።

አለሚቱ፡- “ሁለት መቅረጫ እንግዛ” አለች፡፡

ገብሩ፡- “እኔ ያለኝ ሃምሳ ሳንቲም ብቻ ነው” አለ፡፡

አለሚቱ፡- “እኔ ሁለት ብር እጨምራለሁ” አለች፡፡



ወደነጋዴው ዘንድ አመሩ::

ገብሩ:- “ያንዱ ዋጋ ስንት ነው?” ሲል ጠየቀ::

ነጋዴው:- “ልጆቼ! አገናው ሶስት ብር ነው” አሉ::

አለሚቱ፡- “አገና ምንድን ነው?” አለች።

ነጋዴው፡- “አገና ዋጋ ነው” አሉ። ተከራክረው ሁለት መቅረጫዎች ገዙ።



አለሚቱ፡- “እንሂድ?” አለች፡፡

ገብሩ፡- “እሺ” አለ፡፡

በመጨረሻም ወደቤታቸው ተመለሱ፡፡

USAID
ከአሜሪካን ህዝብ